# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ይሁንታ መድረክ - ዩናይትድ ኪንግደም

## *Ethiopian National Consensus Forum - UK*

*Tel: 0044 (0) 207 589 7212 Ext.(230)*
*Mobile: 07939 956086*

*Email: encfuk@yahoo.co.uk*
*17 Prince's Gate , London ,SW7 1PZ*


ቀን፡ መስከረም 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

## ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ይሁንታ መድረክ

## የተላከ የሐዘን መግለጫ

## ለንደን

በታላቋ ብሪታኒያ የሚገኘው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ይሁንታ መድረክ አባላት በመቀሌ ፖሊስ ኦርኬስትራ አርቲስቶች ላይ በደረሰው ድንገተኛ የመኪና አደጋ ምክንያት ሕይወታቸው የተቀጠፈውን ወገኖቻችን የሕልፈት ዜና የተቀበለው እጅግ በመረረ ሐዘን ድብባ ውስጥ ነው፡፡ እነዚህ ብርቅና ውድ የሕዝብ ልጆች አገራችን ባለፀጋ የሆነችበትን የኪነ ጥበብ ሀብት አንግበው ያገራችን ባህልና ኪነ ጥበብ ለጐረቤት አገር ሕዝቦች በማሳየት ለማስተዋወቅ ጉዞ ላይ እንዳሉ የዚህ አደጋ ሰለባ መሆናቸው ሲሰማ ደግሞ ሐዘናችንን የበለጠ ጥልቅ እንዲሆን አድርጐታል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ይሁንታ መድረክ በዚህ አደጋ ምክንያት ሕይወታቸው ላለፉት ቤተሰቦች መጽናናትን እየተመኘ ያከናውኑት የነበረው የሕዝብ አገልጋይነት ዓላማ በዚህ አደጋ ምክንያት የማይቀለበስ መሆኑን ከመግለጽ ጭምር ነው፡፡

የብሔራዊ ይሁንታ መድረክ
የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
ለንደን